# የኋሊት

በኮስሞስ-2000; Jun2010

ሰጋር ፈረሱን ጫኑ ሰላችሁ
ፈጥኖ ደራሹን ጋልቡ ሰላችሁ
ወደ ፊት የሚል አለ ብያችሁ
የኋሊት ሚሄድ ፈረስ መርጣችሁ
ስት`ጋልቡት በዐይኔ አየኋችሁ።

እርሱን አትጋልቡ ብዬ ብለው
ምክሬ ተንቆ ማን ቢሰማው
ፊታቸው ዞሮ ወደ ጭራው
ሲጋልቡ አየሁኝ በመደዳው።

እንዲያው አንድ እንኳን ልባም ይጠፋል?
እንዲህ ተሁኖ መች ይደረሳል?
ያውም ለትግል ሳይዘጋጁ
እንዲህ ሲኳትን ይያዛል እጁ።